የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ– ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 39
ADDIS ABABA - 23rd May, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፫/፲፱፻፺ ዓ·ም
ለንግድ ሥራ ፈቃድ ማሳደሻ ልዩ የጊዜ ገደብ መፍቀጃ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፯፻፵፯

## CONTENTS

Proclamation No.113/1998
Authorization of a Special Time-limit for Business Licence Renewal Proclamation ................. Page 747

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፫/፲፱፻፺
### ለንግድ ሥራ ፈቃድ ማሳደሻ ልዩ የጊዜ ገደብ ለመፍቀድ የወጣ አዋጅ

የ፲፱፻፺ በጀት ዓመት የንግድ ሥራ ፈቃድ እድሣትን በተመለከተ ልዩ የጊዜ ገደብ መፍቀድ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩)መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለንግድ ሥራ ፈቃድ ማሳደሻ ልዩ የጊዜ ገደብ መፍቀጃ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፫/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ልዩ የጊዜ ገደብ ስለመፈቀዱ</u>

በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፳፭ የተደነገገው ቢኖርም ፤ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማሳደሻ ልዩ የጊዜ ገደብ በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል ።

፫· <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደው ልዩ የጊዜ ገደብ ተፈጻሚነት የሚኖረው ፤ የ፲፱፻፺ በጀት ዓመት የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሣትን በሚመለከት ብቻ ይሆናል።

### PROCLAMATION NO. 113/1998
### A PROCLAMATION TO AUTHORIZE A SPECIAL TIME-LIMIT FOR BUSINESS LICENCE RENEWAL

WHEREAS, it is found appropriate to authorize a special time-limit for the renewal of busniness licences during the 1990 Fiscal Year.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''Authorization of a Speccial Time-limit for Business Licence Renewal Proclamation No. 113/1998.''

2. *Authorization of a Special Time-limit*

Notwithstanding the provisions of Article 25 of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 67/1997, a special time-limit for business licence renewal is hereby authorized.

3. *Scope of Application*

The special time-limit authorized under this Proclamation shall be applicable only in respect of business licence renewals for the 1990 Fiscal Year.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፬. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኃላፊነት</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፣

፩. በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደው ልዩ የጊዜ ገደብ የሚያበቃበትን ወቅት፤

፪. በልዩው የጊዜ ገደብ ውስጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሣት የሚከናወንበትን ዝርዝር የአፈጻጸም ሁኔታ ፣ እና

፫. አግባብ ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮች

መመሪያ በማውጣት ይወስናል ።

፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

4. *Responsibility of the Council of Ministers*

The Council of Ministers shall, by issuing directives, determine:

1) the duration of the special time-limit authorized under this Proclamation;
2) the particulars of execution of business licence renewal within the special time-limit; and
3) other matters of relevance.

5. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 23rd day of May, 1998.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of May, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE